በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትራንስፖርት ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF TRANSPORT

ቁጥር
Ref. No. 1-2/3...
ቀን
Date. 18 ታህሳስ 2010

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA, ETHIOPIIA

ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ መጽደቅን ስለማሳወቅ ይሆናል፣</u>

ሚኒስትር መስሪያ ቤታችን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 እና በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ስራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/1990 ከተሰጠው ስልጣን አንዱ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ማውጣት አንዱ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሰረት በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ በሚኒስትር መስሪያ ቤታችን የጸደቀ መሆኑን እየገለጽን ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የመመሪያውን ኮፒ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

አብዲሳ ያደታ
የራንስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

አባሪ፡- የተጠቀሰው አንድ ጥራዝ

011-551-6166 ፋክስ 011-551 56 65 Fax 1238

# በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ቁጥር 318/2013

ታህሳስ 2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

# በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) እና በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ስራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 7(1) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ለመሰማራት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ቁጥር 318/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. ‹‹የመርክብ ውክልና››፡- ማለት የመርከብ ባለንብረትን፣ ተከራይን፣ ኦፐሬተርን በመወከል መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ መመዝገብን፣ በባህር ወደብ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ለመርከብ አገልግሎት መስጠትን ፣ ዕቃ የመጫን እና የማራገፍን እንዲሁም ዕቃን አጓጉዞ የማከማቸትን ሥራን ማስተባበር እና እና በደንቡ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩ ሥራዎችን ያካትታል፣
2. ‹‹የመርከብ ወኪል›› ማለት በደንቡ መሰረት የመርከብ ውክልና ለመስራት የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፣
3. ‹‹ዕቃ አስተላላፊነት›› ማለት በአገር ውስጥ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ስነ ሥነ ሥርአት፣የወደብ ሥነ ሥርአት እና ሌሎች ስነ ሥርአቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ስራ ይጨምራል፣
4. ‹‹ዕቃ አስተላላፊ›› ማለት በደንቡ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ብቃቱ የተረጋገጠ እና በዘርፉ አገልግሎት ለመስጠት ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport

5. ‹‹የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት›› ማለት የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና የንግድ ሥራ ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፣
6. ‹‹የሥራ ፈቃድ›› ማለት የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ለመሥራት ከንግድ ሚኒስቴር የሚሰጥ ፈቃድ ነው፣
7. ‹‹ አዋጅ ›› ማለት የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነው፤
8. ‹‹ ደንብ ›› ማለት የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፍቃድን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 37/1990 ነው፣
9. ‹‹ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር›› ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣
10. ‹‹ባለሥልጣን›› ማለት በአዋጁ መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፣
11. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
12. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያጠቃልላል፣

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና ሥራ ለመሰማራት በሚፈልግ የብቃት ማረጋገጫ አመልካች እንዲሁም ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አግኝቶ ከሚመለከተዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዘርፉ የንግድ ፍቃድ በማውጣት በሥራዉ ላይ በተሰማራ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

1. የባለሥልጣኑን የቁጥጥር እና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ፣የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓትን ዝርዝርን እና የሚመለከታቸዉ የመንግሥት መ/ቤቶች ኃላፊነት እና ተግባርን ያካተተ ሥርዓት በመዘርጋት ብቃቱ የተረጋገጠ አገልግሎት ሰጪ መፍጠር።
2. ለሚኒስቴሩ በአዋጁ እና በደንቡ በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች ብቃትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መለኪያ መሥፈርት መወሰን።



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

Federal Democratic Republic
Ministry of Transport

3. በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልናን የንግድ ሥራ የሚሰማራ ሰው ከብቃት መለኪያ መሥፈርት በተጨማሪ ሊኖረው የሚገባ ዝርዝር ሙያዊ ሥነ-ምግባር መወሰን፡፡

5. <u>አስፈጻሚ አካል</u>

ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 8፣10፣19 ሥር በተደነገገው መሠረት በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ለመቆጣጠር፣ዝርዝር መመሪያዎችን ለማዘጋጀት፣ ሥራውን ለማስተባበር እና አፈጻጸሙን ለመከታተል በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ መለኪያ መሥፈርት እና ብቁነት</u>

6. <u>ብቁነት</u>

ማንኛውም ሰው በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ለመሰማራት ማመልከቻ ለማቅረብ ብቁ የሚሆነው ፡-

1. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ወይም
2. ኢትዮጵያዊ ካልሆነ አገራችን አንደኛው ወገን ለሚሰጠው ጥቅም ሌላኛው ወገን በተመሳሳይ አፃፋውን የሚሰጥበት የሁለትዮሽ ስምምነት የፈረመችበት አገር ዜግነት ያለው

ከሆነ ብቻ ነው ፡፡

7. <u>የማመልከቻ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት</u>

በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ሥራዎች የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ከማመልከቻው ጋር በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ማያያዝ፣ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላት እና 5 ጉርድ ፎቶግራፎች ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

8. <u>ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅትና  የስራ ልምድ</u>

ማንኛውም ሰው በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ወኪልነት ወይም በሁለቱም ለመሰማራት የሚከተለው ትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ ማሟላት አለበት ፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport
... Democratic Republic ... Ministry of Transport

1. በዓለም አቀፍ ንግድ ወይም በትራንስፖርት ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ በድግሪ የተመረቀ እና ቢያንስ በሚሰማራበት ዘርፍ የ 1 ዓመት ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው ወይም
2. ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ በሎጂስቲክስ ወይም በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተዛማጅ እንደሆነ በተለየ የትምህርት መስክ በዲግሪ የተመረቀ እና ቢያንስ በሚሰማራበት ዘርፍ የ 2 ዓመት ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው ወይም
3. ከቴክኒክ እና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋም በሎጂስቲክስ ወይም በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተዛማጅ እንደሆነ በተለየ የትምህርት መስክ በዲፕሎማ የተመረቀ እና ቢያንስ በሚሰማራበት ዘርፍ የ 4 ዓመት ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው ወይም
4. የዕቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ውክልና ሥልጠና ወስዶ ቢያንስ የማለፊያ ነጥብ ያገኘ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያለው እና ቢያንስ 5 ዓመት ተዣማጅ የሥራ ልምድ ያለው ወይም
5. ከዓለም አቀፍ ንግድ ጋር የተያያዘ አጫጭር ሥልጠናዎችን የወሰደና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያለው እና በዚሁ የሥራ መስክ ወይም ተዛማጅ በሆነ የሥራ መስክ ቢያንስ 5 ዓመት ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው ወይም
6. በባህር ትራንስፖርት የንግድ ግንኙነት ሥራ ጋር የተያያዘ አጫጭር ሥልጠናዎችን የወሰደና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያለውና በዚሁ የሥራ መስክ ወይም ተዛማጅ በሆነ የሥራ መስክ ቢያንስ 5 ዓመት ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው፡፡

9. <u>ካፒታል</u>

1. ማንኛውም ሰው በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ወኪልነት ወይም በሁለቱም ለመሰማራት በደንቡ የተደነገገው ዝቅተኛ መነሻ ካፒታል ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው በዕቃ አስተላላፊነት ብቻ ለመሰማራት ቢያንስ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ካፒታል ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 500,000 ብር (አምስት መቶ ሺህ ብር ) በዓይነት የሚታይ



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport
Ministry of Transport

ሆኖ ለጽ/ቤት እና ለጽ/ቤት አደረጃጀት ማለትም ለፋክስ፣ ለሂሣብ ማሽን፣ለቴሌፎን፣ ለፎቶ ኮፒ፣ ለጽህፈት መሣሪያዎች እና ለአውቶሞቢል የሚወጣ ወጪን ያካትታል፡፡

3. ማንኛውም ሰው በመርከብ ወኪልነት ብቻ ለመሰማራት አንድ ሚሊዮን ብር 1,000,000 ( አንድ ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 300,000( ሶስት መቶ ሺህ ብር) በዓይነት የሚታይ ሆኖ ለጽ/ቤት እና ለጽ/ቤት አደረጃጀት ማለትም ለፋክስ፣ ለሂሣብ ማሽን፣ለቴሌፎን፣ ለፎቶ ኮፒ፣ ለጽህፈት መሣሪያዎች እና ለአውቶሞቢል የወጣ ወጪን ያካትታል፡፡
4. ማንኛውም ሰው በሁለቱም የሥራ መስኮች ላይ ለመሰማራት 2,200,000(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር) ካፒታል ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ) በዓይነት የሚታይ ሆኖ ለጽ/ቤት እና ለጽ/ቤት አደረጃጀት ማለትም ለፋክስ፣ ለሂሣብ ማሽን፣ለቴሌፎን፣ ለፎቶ ኮፒ፣ ለጽህፈት መሣሪያዎች እና ለአውቶሞቢል የሚወጣ ወጪን ያካትታል፡፡
5. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ የተጠየቀው ካፒታል ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የገንዘብ ካፒታል የሚያሳይ የባንክ ደብዳቤ እና የ 3 ወር የባንክ ስቴትመንት ማቅረብ አለበት፡፡

10. <u>አስፈላጊ ባለሙያዎች</u>

1. በዕቃ አስተላላፊነት የሚሰማራ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ ዶክመንት ፕሮሰሰር እና አሰሰር ማለትም ዕቃው የተገዛበት ሰነድ (L/C) ፣ታክስ የተከፈለበት ሠነድ እና የጉምሩክ ሥርዓቶች የተፈፀመበትን ሰነድ የሚያዘጋጅ እንዲሁም በስምንት ቀን ውስጥ መዳረሻ ወደቦች የደረሱ ዕቃዎችን እና በስምንት ቀን ዉስጥ መዳረሻ ወደቦች ያልደረሱ ዕቃዎችን የሚከታተል ፣ የጭነት ዋጋን በግምታዊ ተመን መሰረት አስልቶ የሚያሳውቅ፣ የትራንስፖርት ሠነዶችን የሚያደራጅ፣ የጭነቱን የጉዞ ሂደት እየተከታተለ አስፈላጊውን መረጃ ለደንበኛውም ሆነ ለሌላ አካል የሚያሳውቅ ባለሞያ በቋሚነት መቅጠር አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው በተጨማሪ በዕቃ አስተላላፊነት የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ትራንዚተር ማለትም ዕቃዎቹ በመድረሻ ጣቢያቸው እንደደረሱ ወይም ከደረሱ በኋላ አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት የሚያከናውን እንዲሁም የጉምሩክ ሥነ-



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሬከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

ሥርአት የሚያስፈጽም ትራንዚተር እና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን በቋሚነት መቅጠር አለበት።

3. በመርከብ ወኪልነት የሚሰማራ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ ካንቫሰር እና ቡኪንግ ክለርክ ፣ሺፒንግ ኦፊሰር እንዲሁም በዘርፉ ልምድ ያለውና ለመርከቧ ተገቢው ድጋፍ የሚያደርግ እና ጭነትን የሚያፈላልግ ባለሞያ እና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን በቋሚነት መቅጠር አለበት።

4. በሁለቱም ሥራዎች የሚሰማራ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 ከተጠቀሱት በተጨማሪ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ባለሙያዎችን በቋሚነት መቅጠር አለበት።

11.የጽ/ቤት አደረጃጀት

በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት የሚሰማራ ማንኛውም ሰው አድራሻው የታወቀ ጽ/ቤት ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ጽ/ቤቱም በቴሌፎን፣ፋክስ፣ቴሌክስ፣የሂሣብ መመዝገቢያ ማሽን፣የጽህፈት መሣሪያ ( ኮምፒዩተር፣ፎቶ ኮፒ፣ ፕሪንተር ወ.ዘ.ተ.)፣ ኢንተርኔት ኔትዎርክ ፣ለመረጃ ልውውጥ ባለስልጣኑ የፈቀዳቸውን ሶፍት ዌር ወይም ዌብ ቤዝድ የመገናኛ ዘዴዎችን እና አውቶሞቢል የተደራጀ መሆን አለበት።

12.የጉምሩክ አስተላላፊነት ፍቃድ

1. በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ወኪልነት ወይም በሁለቱም የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ አስተላላፊነት ለመሥራት የሚስችለውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ያኖርበታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ወኪልነት ወይም በሁለቱም የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ አስተላላፊነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ እና በሥራው ላይ የቆየ ስለመሆኑ ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ ካቀረበ ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ አስተላላፊነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አይኖርበትም።



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

13.የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት

በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ስራ የሚሰማራ ሰው መጀመሪያ በንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 105 ላይ የተደነገገው ዝርዝር በተጠበቀ ሁኔታ በንግድ ሚኒስቴር ዋና መዝገብ ማስገባቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ከንግድ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት።

14.ድርጅታዊ ቅርጽ

1. በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ሥራ የሚሰማራ ሰው በአክሲዮን ማኅበር ወይም በሽርክና ማኅበር ወይም በግለሰብ ድርጅት ሊቋቋም ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመርከብ ወኪሉ ወይም የዕቃ አስተላላፊው የተቋቋመው በአክሲዮን ማኅበር ወይም በሽርክና ማኅበር ቅርጽ ከሆነ በንግድ ሕጉ መሰረት በሠነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ የመመሥረቻ ጹሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ አለበት።

15.የሙያ ሥነ-ምግባር

በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ሥራ የሚሰማራ ሰው የሚሰጠው አገልግሎት በሚከተለው የሙያ ሥነ-ምግባር ዓላማ ላይ መመስረት ይኖርበታል፣

1) የተሰማራበትን የሥራ ዘርፍ መልካም ስምና ክብር በሚጠበቅበት እና ከፍ በሚያደርግ አግባብ መስራት፣

2) ሕብረተሰቡ በዘርፉ በሚሰጠው አገልግሎት ጠንካራ እምነት እንዲኖረው ማስቻል፣

3) ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ጥራትን መለያው ያደረገ የተሟላ አገልግሎት መስጠት፣

4) እያንዳንዱ የአገልግሎት ኦፐሬሽን የነፃ ገበያ መርህን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማስቻል።

## ክፍል ሶስት

## ተግባር፣ኃላፊነት እና ሥልጣን

16.የዕቃ አስተላላፊ እና የመርከብ ወኪል ተግባር እና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት ሥራ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፡-



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

1. የኢትዮጲያን ሕግ እና አገሪቱ በዘርፉ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን አውቆና አክብሮ የመስራት፣
2. በዘርፉ የሚገኘን ገበያ በብቸኝነት ለመቆጣጠር በማሰብ ከሚፈጸሙ ማናቸውም ህገ-ወጥ ተግባራት ከመፈጸምም ሆነ ሲፈጸም ከመሳተፍ የመታቀብ፣
3. የንግድ፣ የነፃ ገበያ ውድድር ህግ እና መርህ እንዲሁም አዎንታዊ የንግድ ልማዶችን በማክበር ከሌሎች መሰል አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ለወል ጥቅም በጋራ የመስራት፣
4. በሥራ ምክንያት ያወቀውን የደበኛውን ንግድ እንቅስቃሴ ሚስጢር የመጠበቅ፣
5. ለደንበኛው ወይም ለሌሎች የዘርፉ ተወዳዳሪዎች ወይም ለተቆጣጣሪ መ/ቤት የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ከመስጠት የመታቀብ፣
6. የደንበኛውን ጥቅም በአስጠበቀ መልኩ ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት፣
7. በአገልግሎት አሰጣጡ ከደበኞች የሚቀርቡለት ቅሬታዎች ላይ ተገቢና ፈጣን የእርምት እርምጃ የመውሰድ፣
8. የሚፈጽመውን የሥራ ውል ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲሁም የኢትዮጲያ ሕግ እና ዓለማ አቀፋዊ መሠረታዊ መርህን በማይቃረን መልኩ የመፈጸም፣
9. ከሚፈጽማቸው የሥራ ውል የሚመነጩ ግዴታዎችን በተገቢው ጊዜና የአፈጻጸም ሁኔታ የመተግበር፣
10. ትራንዚት ትራንስፖርቱን ለመቆጣጠር እና ለመደገፍ የወጣ ማናቸውም መመሪያ ላይ የተሰጠውን ተግባር እና ኃላፊነት የመተግበር ፤

17. <u>የባለሥልጣኑ ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጁ ዘርፉን ለመቆጣጠር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ማመልከቻ ላቀረበ አመልካች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ተገቢዉን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት የንግድ ሥራዎች ለመሰማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
2. ከባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ አግኝተዉ በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ወኪልነት ወይም በሁለቱም ሥራዎች የተሰማሩ ሰዎችን ዝርዝር ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲሁም አገሪቷ ለምትገለገልባቸዉ ወደቦች ባለሥልጣን ያሳዉቃል፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሰነድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

3. ባለሥልጣኑ በዉስጥ ዕቅዱ እና ፕሮግራሙ መሠረት ቀደም ሲል መስፈርቱን አሟልተዉ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ አዲስ እና ነባር የእቃ አስተላላፊ እና የመርከብ ወኪሎች ላይ ድንገተኛ ምልከታ በማድረግ ብቃታቸዉን በየጊዜዉ ለማረጋገጥ ተገቢዉን ክትትል ያደርጋል፣

4. ባለሥልጣኑ በሚያደርገዉ ቁጥጥር እና ድንገተኛ ምልከታ በዚህ በመመሪያም ሆነ ትራንዚት ትራንስፖርቱን ለመደገፍ በወጣ ሌላ መመሪያ ወይም አገሪቷ ያጸደቀችው አለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተጣለን ግዴታ መተላለፍ፣ የሞያዉን ሥነ ምግባር መጣስ፣ለሥራዉ ብቁ ያለመሆን፣ በጥንቃቄ መጉደል ምክንያት በደንበኞች ላይ ተደጋጋሚ ጉዳቶችን ማድረስ፣በካፒታልነት ሊኖሩ የሚገቡ የዓይነት እና የጥሬ ገንዘብ መጉደል የመሳሰሉ መሠረታዊ ጉድለቶች ካገኘ የሰጠዉን የእቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ወኪልነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በሚያደርገዉ ቁጥጥር እና ድንገተኛ ምልከታ የሰዉ ኃይል መጓደል፣ የቢሮ አደረጃጀቶች በጊዜያዊ ጥገና ምክንያት መጓደል፣ሪፖርትን በተገቢዉ ጊዜ ያለማቅረብ የመሳሰሉ መሠረታዊ ያልሆኑ ጉድለቶችን ካገኘ ባለሥልጣኑ በሚወስነው አግባብ ያለው የጊዜ ገደብ ጉድለቶችን እንዲያሟላ እና እንዲያርም ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ጉድለቶችን ባያሟላ ወይንም ባያርም የተሰጠዉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰርዝበታል፡፡

6. ባለሥልጣኑ በሚያደርገው ቁጥጥር ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት በሚያደርገው ድንገተኛ ምልከታ ቀደም ሲል በዚህ መመሪያ የተቀመጠዉን መስፈርት አሟልተዉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ የመርከብ ወኪሎችን እና የዕቃ አስተላላፊዎችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲሰርዝ በዚሁ የምስክር ወረቀት መሠረት ያገኙትን የንግድ ፍቃድ እንዲሠረዝ ለንግድ ሚኒስቴር ያሳዉቃል፣ የንግድ ፍቃዳቸዉ መሠረዙንም ይከታተላል እንዲሁም ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና አገሪቷ ለምትገለገልባቸዉ ወደብ ባለሥልጣናት ካስተላለፈው ዝርዝር ውስጥ መሠረዛቸውን ያሳዉቃል፡፡



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

7. ባለሥልጣኑ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ወኪልነት የንግድ ሥራዎች የብቃት ማረጋገጫን የመሰረዝ ዉሳኔ ሲያሳልፍ ዉሳኔዉን በዝርዝር ምክንያት በማስደገፍ የብቃት ማረጋገጫዉ መሰረዙን በጹሁፍ ለዕቃ አስተላላፊው ወይም ለመርከብ ወኪሉ ያሳውቃል፡፡

18.የሚኒስቴሩ ተግባር እና ኃላፊነት

1. የመመሪያውን አፈጻጸም ይከታተላል፣ በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት ይገመግማል፣አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል እንዲሁም እርማት በሚያስፈልጋቸው የአፈጻጸም ችግርች ላይ አቅጣጫ ይሰጣል፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 መሠረት በባለሥልጣኑ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ የሚሰጥ ኮሚቴ በሥሩ ያዋቅራል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19.የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1. የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ወይም የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው በኂላ በተደረገ ቁጥጥር እና ድንገተኛ ፍተሻ የብቃት ማረጋገጫው እንዲሰረዝ በባለስልጣኑ ውሳኔ የተሰጠበት ሰው በዉሳኔው ቅሬታ ካለው ለሚኒስቴሩ ይግባኝ ማለት ይችላል ፣
2. በባለስልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ቅሬታውን በጹሁፍ በመግለጽ እና በማስረጃ በማስደገፍ የባለሥልጣኑ ዉሳኔ በጹሁፍ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡
3. በውሳኔው ቅር የተሰኘ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ካላቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም በቂ ምክንያት ያቀረበ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው ጊዜ በኂላ ቅሬታውን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡
5. ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 በተዋቀረው ኮሚቴ አማካኝነት የቀረበው ይግባኝ የሚያስቀርብ ወይም የማያስቀርብ መሆኑን ይለያል፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

በሚያስቀርበው ላይ ተገቢዉን ምርመራ ያካሂዳል፣መቅረብ ያለባቸዉ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይሰጣል። ፣ዉሳኔዉ ተገቢ ነዉ ብሎ ካመነ የባለሥልጣኑን ዉሳኔ ያጸድቃል፣የባለሥልጣኑ ዉሳኔዉ ተገቢ አይደለም ብሎ በአመነ ጊዜ በባለሥልጣኑ የተሰጠዉን ዉሳኔ ይሽራል ያሻሽላል።

6. በዚህ አንቀጽ መሰረት በሚኒስቴሩ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል።

20. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህ መመሪያ መሻሻል አለበት ብሎ በአመነ ጊዜ ሁሉ ሊያሻሽለዉ ይችላል።

21.የተሻረ መመሪያ

በ 1992 ዓ.ም የወጣው የአጠቃላይ የዕቃ አስተላላፊነት/ ፍሬይት ፎርዋርዲንግ/ እና የመርከብ ውክልና በተመለከተ በትራንስፖርት እና መገናኛ ሚኒስቴር ስለ ችሎታ ማረጋገጫ የወጣ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

22. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ታህሳስ/ 16 ቀን 2010 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport